በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊከ
የከተማና መሰረተልማት ሚኒስቴር



# መደመር
## በኮንስትራክሽን

# መደመር በኮንስትራክሽን

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊከ
የከተማና መሰረተልማት ሚኒስቴር

ግንቦት 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መደመር በኮንስትራክሽን

©

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊከ
የከተማና መሰረተልማት ሚኒስቴር

ግንቦት 2017 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ 5

መነሻ 7

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሀገራዊ ፋይዳ 10

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የብቸኝነት ጉድለት ማሳያዎች 12

መደመር በኮንስትራክሽን 24

የኮሪደር ልማት እንደ የመደመር እሳቤ ውጤት 31

# ማውጫ


የተደማሪነት ሳንካዎች በኮንስትራክሽን 33

በመደመር እሳቤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተልዕኮ 39

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ በመደመር እሳቤ ተቃኝተው ሊተገበሩ የሚችሉ ኢኒሺየቲቮች 42

ማጠቃለያ 51

# መነሻ

1

ኢትዮጵያ በሁሉም ረገድ ሊባል በሚቻል ደረጃ በወሳኝ የታሪክ እጥፋት ላይ ትገኛለች። በረጅም የሀገረ መንግስትነት ታሪኳ ከመጣችበት መንገድ በመሰረታዊነት እና በፍጥነት ወደ አዲስ ምዕራፍ እየተሸጋገረች ነው። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው እንዲሁም በማህበራዊ ዘርፍ ወሳኝ የሚባሉ ለውጦች እየተካሄዱ ነው። መንግስት ሁሉንም ያሳተፈ፣ ፍትሃዊ እና የበለፀገች ሀገር ለመገንባት "በሁሉም፣ ከሁሉም፣ለሁሉም የሆነች ኢትዮጵያ!" በሚል መሰረታዊ እሳቤና መርህ በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ ምህዳር ላይ ሰፋፊ ማሻሻያዎች አድርጓል።

በተለይም ፖለቲካችንን ከተለመደው የሴራ፣ የቂም በቀል፣ የጽንፍ እና በጨቋኝ ተጨቋኝ ነጠላ ትርክት የተቃኘ አስተሳሰብ በማላቀቅ የሀሳብ ልዕልናን ማዕከል ወዳደረገ፣ ምህዳሩንም ወትሮ ከነበረው የሰፋና በርካታ ዕድሎችን የሚሰጥ በማድረግ የሃገራችንን የፖለቲካ ባህል፣ የዲሞክራሲ ስርዓት፣ የሀገረ መንግስት እና ብሄረ መንግስት ግንባታ ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚያስችል አስቻይ ሁኔታና አስተማማኝ መሰረት ተጥሏል።

በተመሳሳይ፣ በሁለት ዙር በተተገበሩ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች የተገኙ ተሞክሮዎችን በማጠናከር መሰረታዊ የአስተሳሰብና የአካሄድ ለውጥ ተደርጎበት የተተገበረው ሁለንተናዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገበበት ያለ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት ከዓለም ኢኮኖሚ ጋር ለመዋሀድ ተቸግሮ፣ ተነጥሎና ዝግ ሆኖ የቆየውን ኢኮኖሚ በመክፈት የሀገራችንን ብልጽግና ለማረጋገጥ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ወሳኝ እርምጃ መሆኑ በተጨባጭ እየታየ ነው።

ይህ የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ እና እየተመዘገበ ያለው ውጤት፣ በፍርሀት ከመቀፍደድ እና በስጋት ከማፈግፈግ ይልቅ የቀጣናችንንና የዓለምን እውነታ በቅጡ በመረዳት ፊት ለፊት ተጋፍጦ መሻገርን፣ ከአጭር ጊዜ ተግዳሮቶች ይልቅ የረጅም ጊዜ ጥቅሞችን ማስቀደምን፣ ሀገራችን ያላትን እምቅ አቅም ተረድቶ ከተኛንበት ጥልቅ እንቅልፍ መንቃትን፣ የጥቂቶችን ፍላጎት ከማስከበር ይልቅ ለአብዛኛው ህብረተሰብ ዘላቂ ተጠቃሚነትመስራትን እንዲሁም መንግስት ለኢትዮጵያብልፅግና ያለው ጥልቅ ፍላጎት፣ ዝግጁነት እና ቁርጠኝነት የታየበት ነው።

በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ እንደ መንግስት የተወሰዱ እና እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች የተለመደው አይነት መደበኛ ማሻሻያዎች አይደሉም። በግብርና፣ በማዕድን፣ በኢንዱስትሪ፣ በቴክኖሎጂ እና በቱሪዝም ዘርፍ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችም የተለመደው አይነት ምርትን የማሳደግ ውጥኖች ብቻ አይደሉም።

በአጠቃላይ በተለያዩ ዘርፎች እየተሰሩያሉ ሥራዎች መሰረታዊ የአስተሳሰብ፣ የአካሄድ እና የድርጊት ለውጥ የሚያስከትሉ፣ የሀገረ መንግስት እና ብሄረ መንግስት ግንባታችንን በጽኑ መሠረት ላይ የሚያቆሙ፣ የሀገራችንን ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እና እመርታ የሚያረጋግጡ፣ የአሁኑን እና የሚመጣውን ትውልድ እጣ ፈንታ የሚወስኑ ወሳኝ ሥራዎች ናቸው።

በዚህ ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍና ሀገራዊ የለውጥ ጉዞ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ጉልህ እና የማይተካ ሚና የሚኖረው ሲሆን ይህ ጽሁፍ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሚና መወጣት እንዲችል በ″መደመር″ እሳቤ ሊቃኝ፣ ሊዋቀር፣ ሊንቀሳቀስ እና ሊመራ እንደሚገባ ያሳያል።

# የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሀገራዊ ፋይዳ

2

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ነው። በተለይም ለአገር ውስጥ ጥቅል ምርት፣ የሥራ እድል ፈጠራ፣ ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለመዋቅራዊ ሽግግር እና ለዜጎች ሁለንተናዊ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ወሳኝ ነው። ዘርፉ በአሁኑ ሰዓት በአማካይ ወደ 20 በመቶ የሚጠጋውን አጠቃላይ የአገር ውስጥ ጥቅል ምርት አስተዋፅኦ የሚያደርግ፣ ከ 10 በመቶ በላይ ለሚሆነው አምራች የማህበረሰብ ክፍል በቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሰፊ የስራ ዕድልን የሚፈጥር፣ ከ35,000 በላይ ከፍተኛና አነስተኛ ደረጃ ያላቸውን ኩባንያዎች እና ከ140 ሺ በላይ የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ያቀፈ፣ የሀገራችንን ገጽታ እና የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ በመሰረታዊነት እየቀየረ ያለ፣ ከፍተኛ የማደግ አቅም ያለው እና በቀጣይ ዓመታት በተከታታይ ከ10 በመቶ በላይ አማካይ ዓመታዊ እድገት እንደሚያስመዘግብ የሚጠበቅ ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንዱስትሪው ከዚህ በላይ ሚናውን እንዳይወጣ የተለያዩ መዋቅራዊ እና ከአፈፃፀም ጋር የተያያዙ ውስብስብ ችግሮች ያሉበት፣ በአብዛኛው ልማዳዊ አሠራርን የሚከተል ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኢንዱስትሪው ከመንግሥትና ከግሉ ዘርፍ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት እና ኢኮኖሚውን ከጫፍ እስከ ጫፍ በቀላሉ ማነቃነቅ እና ማነቃቃት እንደ ሀገር የምንፈልገውን አዎንታዊ ሰላም በማስፈን ረገድ መንግስት እያደረገ ላለው ጥረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክትየሚችል ዘርፍ ነው። በመሆኑም አሁን ላይ የሚስተዋሉ የአሰራርም ሆነ መዋቅራዊ ችግሮች ደረጃ በደረጃ እና በተጠና አግባብ በመፍታት እንዲሁም ዘርፉ የሚንቀሳቀስበትን ግልጽ እሳቤና አቅጣጫ አስቀምጦ በመደመር እሳቤ በመምራት ለሀገራችን የብልጽግና ጉዞ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ማበርከት ይቻላል።

# የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የብቸኝነት ጉድለት ማሳያዎች

3

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የህዝባችንን የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻልም ሆነ የሀገራችንን ብልጽግና ከማረጋገጥ አኳያ ጉልህ እና የማይተካ ሚና አለው። ሆኖም በዘርፉ የሚደረገው ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የውጤታማነት እና የብቃት (Investment Efficiency and Effectiveness) ጥያቄ የሚነሳበት ነው። ከዚህ አኳያ ፕሮጀክቶች ሲተገበሩ ሊወጣባቸው ከሚገባ በላይ የተጋነነ ወጪ የሚያስወጡ መሆናቸው እና ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የተገነቡ መሰረተልማቶች በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት የታለመላቸውን ዓላማ እና ግብ በሚጠበቀው ልክ ሳያሳኩ የሚቀሩበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ የሚታይ እውነታ ነው። ለዚህም እንደ አዲስ አበባ ጅቡቲ የባቡር መስመር፣ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር፣ የመስኖና ግድብ ፕሮጀክቶች፣ የስኳር ፕሮጀክቶች፣ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተጀመሩ የህንጻ ግንባታ ፐሮጀክቶች፣ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የተገነቡና የሚጠበቀውን ያህል የትራፊክ መጠን የማያስተናግዱ የአስፋልት መንገዶች ወ.ዘ.ተ. ይጠቀሳሉ። በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚታየው የኢንቨስትመንት ውጤታማነት እና ብቃት ጉድለት የህመሙ ውጤት ሲሆን እነዚህ እውነታዎችና ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ተጨማሪ ማሳያዎች የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የብቸኝነት ጉድለት ተጠቂ ለመሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው።

## 3.1. በጋራ ሀገራዊ ግብ እና ብሔራዊ ኃላፊነት ስሜት አለመንቀሳቀስ

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታን፣ የ10 ዓመት የዘርፍ እቅድን እና የ3 ዓመት የመካከለኛ ዘመን እቅድን ጨምሮ በዘርፉ እንዲሳኩ የሚጠበቁ የተለያዩ ግቦችን ያካተቱ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ ሰነዶች ኢንዱስትሪው የደረሰበትን የእድገት ደረጃ፣ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ እና እያጋጠመው የሚገኘውን ተግዳሮቶች በመለየት፣ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማመላከት እንዲሁም ዝርዝር ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በማመላከት በኩል የማይተካ ሚና ተጫውተዋል። ሆኖም ግን በዘርፉ የተለያየ ሚና እና ድርሻ ያላቸው አካላት ግልጽ የጋራ ግብ ኖሯቸው ይህን የጋራ ግብ ለማሳካት በቅንጅት እና በትብብር ሲሰሩ አይስተዋልም።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ኩባንያዎች ከረጅም ጊዜ ሀገራዊ ጥቅም እና ከያገባኛል መንፈስ ይልቅ የአጭር ጊዜ የግል ትርፋቸውን ሲያስቀድሙ ማየት የተለመደ ነው። በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት የሚስተዋሉ ከደረጃ በታች የሆኑ እቃዎችን ወይም ግብአቶችን መጠቀም የዚህ አንዱ ማሳያ ሲሆን በፕሮጀክት ትግበራ የሚሳተፉ አካላትን በትናንሽ መደለያ በመደለል ከሚጠበቀው የጥራት ደረጃ አሳንሶ መፈጸምም የዚሁ ነጸብራቅ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሀገራችን በግንባታው ዘርፍ የተሰማሩ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች እና መንግስትንና ህዝብን ወክለው ፕሮጀክት የሚመሩ አካላት ሥራቸውን እንደ ብሔራዊ (ሀገራዊ) ኃላፊነት ወስደው ከማስፈጸም አንጻር ክፍተት ይስተዋልባቸዋል።

ይልቁንም ድርጅቶቹ ራሳቸውን እንደ አገር ገንቢዎች ሳይሆን ዓላማው ትርፍ ብቻ እንደሆነ አካል ይቆጥራሉ። በተመሳሳይ ፕሮጀክት የሚያስተዳድሩ አካላት ፕሮጀክቱ የአገር ግንባታ ወሳኝ ተግባር መሆኑን በመዘንጋት በአግባቡ ተተግብሮ ለአገር ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ በሂደቱ በግል ሊገኝ በሚችል ጊዜያዊ ትርፍ ሲጠለፉ ይታያል። እንደ መንግስትም በሂደቱ የሚሳተፉ አካላትን ጠርቶ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ከኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ እድገት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ከማስረዳት፣ በየደረጃው ግልጽ ብሔራዊ (ሀገራዊ) ኃላፊነት ከመስጠት እንዲሁም ይህን ኃላፊነት አለመወጣት የሚያስከትለውን መዘዝ ከማስገንዘብም ሆነ ተገቢውን እርምጃ ከመውሰድ አኳያ ሰፊ ክፍተት ይታያል።

# 3.2. የመናበብ፣ ቅንጅት እና ትብብር ውስንነት

## 3.2.1 በፕሮጀክት የትግበራ ሂደት ደረጃዎች የሚስተዋል ጉድለት እና የመናበብ ውስንነት

በሀገራችን ፕሮጀክቶችን በማስፈጸም ሂደት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች (ከፕሮጀክት ልየታ እስከ ሀብት አስተዳደር) የሚከሰቱ የመናበብ ውስንነቶች የተለመዱ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የሚታየው የመጀመሪያው ጉዳይ የፕሮጀክት ልየታ እና ዝግጅት ከሀገራዊ እቅድና ግብ ጋር በበቂ ደረጃ አለመናበብ እና አለመጣጣም ነው፡፡ የልማት ፕሮጀክቶች ምርጫና ቅደም ተከተል በአብዛኛው ሀገራዊ እቅድን ካገናዘበ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኒካዊ አዋጭነት ጥናት ሳይሆን በቁንጽል አካባቢያዊ እይታ ወይም በፖለቲካ ውሳኔ ሲሆን መሰል ችግሮች መፈጠራቸው አይቀሬ ነው፡፡ በተመሳሳይ፣ ለግንባታ የተለዩ ፕሮጀክቶች በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው ዲዛይናቸው ካልተሰራ እና በግዥ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገ በትግበራ እና በሀብት አስተዳደር ወቅት ችግር ማጋጠሙ አይቀሬ ነው፡፡ በዓለም ላይ የፕሮጀክት አፈጻጸም ብቃት ደረጃን ለመለካት በስፋት ጥቅም ላይ ከሚውሉ መለኪያዎች ውስጥ የፕሮጀክት ማኔጅመንት የብስለት ደረጃ አንዱ ሲሆን በዚህ መለኪያ መሰረት የአብዛኛዎቹ የሃገራችን ተቋማት የፕሮጀክት ማኔጅመንት የብስለት ደረጃ ዝቅተኛ የሚባል (ከአምስት ሁለት እና ከሁለት በታች) ነው፡፡ ይህ በፕሮጀክት ትግበራ ኡደት ደረጃዎች መካከል የሚስተዋል ጉድለት እና አጠቃላይ የፕሮጀክት ማኔጅመንት የብስለት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን የፕሮጀክት አፈጻጸምን በቀጥታ እና በሁሉም መልኩ ይጎዳል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱን የፕሮጀክት ትግበራ ደረጃ በመደመር ቅኝት ከቀጣዩ ደረጃ ጋር በማስተሳሰር እና በማቀናጀት የፕሮጀክት አፈጻጸምን ውጤታማነት ማሻሻል ይቻላል።

### 3.2.2. በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚስተዋል የመናበብ፣ ቅንጅት እና ትብብር ውስንነት

በተደጋጋሚ እንደሚገለጸው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በርካታ ባለሚና እና ባለድርሻ አካላት ያሉበት ነው። በእነዚህ አካላት መካካል ያለው ግንኙነት ደካማና ያልተቀናጀ ብቻ ሳይሆን ከትብብር ይልቅ መገፋፋት የሚስተዋልበት በመሆኑ እንደ ሀገር በዘርፉ ያለውን አቅም ማሰባሰብና የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም። የዘርፉ ቁልፍ ተዋንያን ከሚባሉት ውስጥ በባለቤት (በአሰሪ)፣ በተቋራጭ እና በአማካሪ መካከል ያለውን ግንኙነት ስንመለከት በአብዛኛው ተግባብቶ እና ለጋራ ግብ ተባብሮ ከመስራት ይልቅ መጠራጠር፣ መጠላለፍ እና በባላንጣነት የመተያየት ዝንባሌ ያይላል፤ ከመተማመን ይልቅ አለመተማመን፣ ለጋራ ግብናጥቅም በትብብር ከመስራት ይልቅ የአንዱ ትርፍ የሌላው ኪሳራ ሆኖ የጥቅም አለመጣጣምና ግጭት ይስተዋላል። ይህ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚስተዋል በተናጥል እውነት ላይ መቸንከር እና የሌላውን ወገን እውነት ለማየት ዝግጁ አለመሆን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አንዱ ጉድለት እና ስብራት ነው። የጋራ ግብን አሳንሶ፣ የተናጥል ግብን አግዝፎ የማየት በሽታ ኢንዱስትሪውንም ሆነ ሀገርን ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል። ከዚህም ባለፈ በእነዚህ አካላት መካከል መብትና ግዴታን ማዕከል ያደረገ ግልጽ የሥራ ግንኙነት ሳይሆን መብትን አሳልፎ የሚሰጥ፣ ግዴታንም ከተቻለ ሸሽጎ ካልሆነም የእጅ መንሻ ሰጥቶ በይፋ የሚያሳልፍ ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት እንዳለ በተደጋጋሚ የሚገለጽ እና የአደባባይ ሚስጥር ተደርጎ የሚወሰድ ጉዳይ ነው።

ከላይ የቀረበው የተዛባ አስተሳሰብ እና ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት እንዲሁም የወል እውነትን ከማጽናት ይልቅ በተናጥል እውነቶች ላይ በመንጠልጠል ጽንፍ አቋም መያዝ፤ ዘርፉ መሰረታዊ የሆነ የቅኝት ችግር እንዳለበት ማሳያ ነው። ይህ መሰረታዊ ችግር ሳይፈታና የጋራ ግባችን ላይ መግባባት ሳይፈጠር በዘርፉ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ጥረት በሙሉ በሙዚቃው ዓለም እንደሚባለው 'በትዝታ ቅኝት አምባሰልን ለመጫወት እንደመሞከር' የሚቆጠር እና መቼም የማይሳካ ከንቱ ልፋት ነው። በመሆኑም ጫወታው እንዲስተካከል በቅድሚያ ይህን የቅኝት መፋለስ ማስተካከል እና ፈር ማስያዝ ያስፈልጋል።

### 3.2.3 በመንግስት አካላት መካከል የሚስተዋል የመናበብ፣ ቅንጅት እና ትብብር ውስንነት

በፕሮጀክት ትግበራም ሆነ በኮንስትራክሽን ኢንዱስቱሪው ጤናማነት፣ ተወዳዳሪነትና እድገት መንግስት የማይተካ ሚና አለው። የመንግስት አካላት ተብለው የተወሰዱት በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ በተዋረድ የሚገኙ የአስተዳደርና የመንግስት አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች በትይዩ የሚገኙ የሴክተር ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና የመንግስት ተቋማት ናቸው። ከፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም አኳያ በእነዚህ አካላት የሚስተዋል የጎንዮሽ እና የተዋረድ አለመናበብ፣ አለመቀናጀት እና አለመተባበር በግልጽ የማይታይ ሆኖም ከፍተኛ ጉዳት እና ኪሳራ እያደረሰ የሚገኝ ጉዳይ ነው። በተለይም በፌደራል ደረጃ የሚያዙ የመሰረተ ልማት እና ሌሎች የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን በሁሉም ደረጃ ያሉ የመንግስት አካላት ፕሮጀክቶቹን እንደ ሀገራዊ ፕሮጀክት በመውሰድ የሚያሳዩት ትብብር እና ድጋፍ በአብዛኛው ዝቅተኛ ነው።

# 3.3. ሀገራዊ መነሻ ወረትን በአግባቡ አለመረዳት እና አለመጠቀም

## 3.3.1. በዘርፉ ያለው ሀገር በቀል እውቀትና ልምድ ትውልዶችን መሻገር አለመቻሉ

ኢትዮጵያ ዘመናትን ያስቆጠረ ሀገር በቀል የግንባታ እውቀትና ልምድ እንደነበራት እምብዛም የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፤ ትውልዶችን ተሻግረው አሁን ድረስ የቆሙ ግንባታዎች የዚህ እውነታ ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው። ይህ ልዩ የግንባታ ጥበብ ከአደባባዮች እስከ ቤተመቅደሶች፣ ከቤተ መንግስቶች እስከ የንጉሳዊ መኖሪያ ቤቶች፣ ከሀውልቶች እስከ ድልድዮች፣ ከዘመናዊ ኪነ ህንጻዎች እስከ ባህላዊ ጎጆዎች ድረስ ይዘልቃል። የላሊበላን ውቅር አብያተ ቤተክርስቲያናት፣ በጎንደር አብያተ መንግስታት ግቢ ውስጥ ያሉ የኪነ-ህንፃ ውጤቶችን፣ የአክሱም ሀውልትን፣ በ9ኛው ክፍለ ዘመን የተገነባው የጀጎል ግንብ፣ በ16ኛው እና 17ኛዉ መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ መሰራታቸው የሚነገርላቸውን የተለያዩ ድልድዮች እና በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚሰሩ ባህላዊ ቤቶችን ብንመለከት የዚህ ማሳያ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው። እነዚህ የግንባታ ውጤቶች ታሪክ የማይሸራቸው እና ትውልድ የሚኮራባቸው ታሪኮች ብቻ ሳይሆኑ ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ቋሚ መዘክርም ናቸው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊና ባህላዊ የግንባታ እውቀት የተለየ የሆነ የሥነ ጥበብ፣ የሂሳብ እና የተፈጥሮ ሳይንስ ውህደት የነበረው ቢሆንም ከግንባታዎቹ በተጻራሪ እነዚህን አስደናቂ የግንባታና የኪነ ህንፃ ውጤቶች ያስገኘልን ሀገር በቀል እሳቤ፣ እውቀት፣ ትጋትና ልምድ ዘመናትን ሊሻገር እና በትውልድ ቅብብሎሽ ሊዳብር እና ሊጎለብት አልቻለም። ቴክኖሎጂ በቅጡ ባልዳበረበት ዘመን አስደናቂ እና ዘመን ተሻጋሪ የግንባታ ውጤቶች ተሰርተው አሁን በዚህ ዘመን በከፍተኛ ትምህርት እውቀት፣ በዘመናዊ መሳሪያዎች፣ ግብአቶች እና ቴክኖሎጂ እየታገዙ የሚሰሩ የግንባታ ስራዎች የጥራት ችግር የሚስተዋልባቸው፣ ውበታቸው ፈጥኖ የሚደበዝዝ እና የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ መሆናቸው ችግሩ የሚጀምረው ከአስተሳሰብ እና ለጥራት ከሚሰጥ ዋጋ መሆኑን ያመላክታሉ። ከዚህም ባሻገር በቀደሙት የግንባታም ሆነ የኪነ ህንጻ ውጤቶች ያለውን እውቀት እና ልምድ መርምሮ፣ ቀምሮ እና አጎልብቶ ለመጠቀም የተደረገው ጥረት ውስን መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### 3.3.2. የሀገር ውስጥ የግንባታ ግብአቶችን በተገቢው መንገድ አለመጠቀም

ሀገራችን ብዙ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሯትም፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በአብዛኛው ከውጭ ሀገር በሚገቡ ግብአቶች እና በውጭ ሀገር የሚመረቱ የግንባታ እቃዎች ላይ ጥገኛ ነው። በተለይም እንደ ብረት፣ የኤሌክትሪክ እቃዎች፣ ቀለም፣ ግራናይት፣ ሴራሚክ እና ሌሎች የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎችን በስፋት ከውጭ እያመጣን ነው። ለዚህም አገራችን በየዓመቱ እስከ 1.2 ቢሊዮን ዶላር እና ከዚያ በላይ ታወጣለች። ይህ ጥገኛነት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት የሚጎዳ ከመሆኑ

ባሻገር የአገር ውስጥ አምራቾችን አቅምና ተወዳዳሪነት እና ሰፊ የሥራ ዕድል የመፍጠር እድልን በማዳከም ኢኮኖሚውን በዘላቂነት ይጎዳል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሀገራችን ውስጥ በብዛት የሚገኙ የግንባታ ማቴሪያሎችን (ቀርከሃ/ባምቡ፣ እንጨት እና እንደ ጣውላ ያሉ የእንጨት ውጤቶች፣ ድንጋይ፣ አፈር፣ የተለያዩ ተረፈ ምርቶች፣ ወ.ዘ.ተ.) በማውጣት ለቤቶች እና የተለያዩ መሠረተ ልማት ስራዎች በአግባቡ እና በስፋት መጠቀም የሚቻል ቢሆንም በዚህ ረገድ በተግባር የሚታየው እውነታ ውስን እንዲሁም በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በቀላል ማሽነሪዎች እና በውጤታማ የግንባታ ስልቶች የታገዘ አይደለም። በሀገር በቀል የግንባታ እውቀት እና ዘዴዎች ላይ የተወሰኑ በቀላል ማሽነሪዎች የታገዙ ሥራዎችን በማከል፣ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸውን ሥራ ፈጣሪዎች በማበረታታት እና የገበያ ትስስር በመፍጠር በየአካባቢው ያሉ ጸጋዎችን ወደ ሀብት መቀየር እንዲሁም በተጨባጭ መሬት ላይ ያሉ የህብረተሰብ ችግሮችን ማቃለል፣ የተሻለ የኑሮ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።

## 3.4. የፖለቲካ ገበያ ቦታ

የፖለቲካ ገበያ ቦታ ኢትዮጵያን በድህነት አዙሪት ውስጥ የሚያቆይ ብቻ ሳይሆን የመንግስታዊ ስርዓቱ ስጋት መሆን የሚችል አደገኛ ሁኔታ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ይገለጻል። ሆኖም ጽንሰ ሀሳቡን በጥልቀት ተረድቶ፣ ሁኔታው አገር ላይ ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ በአግባቡ አጥንቶና ተገንዝቦ ተገቢውን የመከላከል እርምጃ ከመውሰድ አንጻር የተኬደው ርቀት በቂ ነው ለማለት አያስደፍርም። በተለይም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከሚያንቀሳቅሰው የሀብት መጠን አንጻር ምቹ የፖለቲካ ገበያ ቦታ ሆኖ የማገልገል ሰፊ እድል ያለው ነው።

ፖለቲከኞች ለተለያዩ መሰረተልማቶች እና ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎች የሚመደበውን ከፍተኛ የመንግስት በጀት አጠቃቀም እንዲሁም የግንባታ ፕሮጀክቶችን ትግበራ ከዘላቂ አገራዊ ጥቅም ይልቅ የድጋፍ መሰረታቸውን ለማጠናከር ወይም በምርጫ ድጋፍ ለማግኘት ከተጠቀሙበት፣ በሂደቱም ተቋማት ላይ ይፋዊ እና ይፋዊ ያልሆነ ጫና ካሳደሩ የፖለቲካ ገበያ ቦታ ይፈጠራል። በዚህም ፖለቲከኞች ወይም የተወሰኑ ቡድኖች ተቋማዊ እና ህጋዊ ስርዓቱን ጠብቆ ፈሰስ በተደረገ በጀት የፖለቲካ አቅማቸውን ያጠናክራሉ፣ ይህ የሀብት ፍሰት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካም ተቋማዊ ነጻነትን፣ ግልጸኝነትን እና ተጠያቂነትን ያዳክማል።

የሀገራችን የግንባታ ዘርፍ የተወሳሰበ የፖለቲካ ገበያ ቦታ ሊሆን እንደሚችል አለመገመት የዋህነት ነው። በየደረጃው ያሉ ፖለቲከኞች የተሰጣቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት ዘንግተው የተወለዱበትንና የወከሉትን አካባቢ ጥቅምና ፍላጎት ብቻ የሚያራምዱ ከሆነ፣ የዘርፉ ተዋንያን ትላልቅ ኮንትራቶችን ለማግኘት ከፖለቲከኞች ጋር የሚኖር ግንኙነት ወሳኝ ነው ብለው ካመኑ ወይም ውስን ኩባንያዎች በቀላሉ የተለያዩ ኮንትራቶችን ሲያገኙ እና ብዙሃኑ ስራ አጥተው ሲቸገሩ ማየት የተለመደ ሁኔታ ከሆነ ለፖለቲካ ገበያ ቦታ ማበብ የሚመች ከባቢ መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። እነዚህ መገለጫዎች አሁን ላይ በተጨባጭ የሚስተዋሉ ስለመሆናቸው አመላካች ጉዳዮች አሉ።

ከዚሁ ጋር በተወሰነ መልኩ የሚያያዘው በሀገራችን ዘላቂ ወይንም ዘመን ተሻጋሪ የሥራ ተቋራጮች እንዳይፈጠሩ መሆናቸው ነው። በተለያየ ወቅት የሚፈጠሩ እና ጎልተው የሚወጡ የሥራ ተቋራጮች ከፖለቲካ ስርዓቱ እና በየወቅቱ ከሚኖሩ ፖለቲከኞች ጋር ቁርኝት ሲኖራቸው የሚስተዋል ሲሆን ይህም ፖለቲካው ላይ ለውጥ ሲመጣ አብሮ የመጥፋት ሁኔታ በሰፊው እንዲለመድ አድርጓል። ይህም በሌሎች የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪያቸው ካደገ አገራት ከተለመደው በተጻራሪ በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ከአንድ ትውልድ በላይ የዘለለ እድሜ ያላቸው የስራ ተቋራጮች ወይም የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እንዳይኖር አድርጓል። ይህ ጉዳይ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አካባቢ ጭምር የሚስተዋል ነው። ይህ እውነታ በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለሚስተዋለው የውድድር መዛባት፣ የተወሰኑ የሥራ ተቋራጮች ከአቅም በላይ ፕሮጀክቶችን መያዝ፣ የፕሮጀክት መዘግየት፣ ዋጋ መናር፣ የግንባታ ጥራት መጓደል እና የልማት ስርጭት በሚፈለገው ልክ አለመመጣጠን የራሱን ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በሌላ በኩል በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችን በገንዘብ እና በማቴሪያል ከመደገፍ አንጻር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እና ፕሮጀክቶች ወሳኝ የሀብት ምንጭ ስለመሆናቸውም በስፋት የሚነገር ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ፣ የፖለቲካ በጀት ሲገኝ ብቻ ሳይሆን ሲጠፋ እና ሲቀንስም የግጭት መፈልፈያ ሊሆን እንደሚችል መዘንጋት የለበትም። በመሆኑም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ የፖለቲካ ገበያ ቦታ ጉዳይ ጠለቅ ያለ ትንተና ተካሂዶበት ተገቢው የመቀልበሻ ስትራቴጂ ካልተዘጋጀለት አሁን በዘርፉ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን የበለጠ የማወሳሰብ እንዲሁም ሳይፈቱ ለተራዘመ ጊዜ እንዲቆዩ የማድረግ አቅም አለው።

# መደመር በኮንስትራክሽን

4

## 4.1. የመደመር ብያኔ በኮንስትራክሽን

መደመር የማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ዘርፎችን ጨምሮ ሁሉንም ግላዊና ማህበረሰባዊ የህይወት ዘይቤን የሚነካ እሳቤ ነው። አላባዎቹም ሀገራችን ኢትዮጵያ ልትሄድበትና ልትደርስበት የሚገቡ መንገዶችና መዳረሻዎች ሲሆኑ ለእሳቤው መዳበር ገፊ ምክንያቶች ዘላቂና አፋጣኝ መፍትሄ የሚፈልጉ ሀገራዊ ተግዳሮቶች ናቸው። በመሆኑም የመደመር እሳቤ የሀገራችንን ተጨባጭ ችግሮችና ነባራዊ ሁኔታዎች መሰረት ያደረገ ነው ። የዕሳቤው ምንጭ ሀገራዊ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታዎች በመሆናቸው ለመደመር የሚሰጠው ትርጓሜም ከዚሁ ተጨባጭ ሁኔታ የሚመነጭ ነው ። የመደመር ዋነኛ አላማ ሀገራችን ባለፉት አመታት ያስመዘገበቻቸውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድሎች ጠብቆ ማስፋት፣ የተሰሩ ስህተቶችን ማረም እንዲሁም የመፃዒውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት ማሳካት ነው። በመሆኑም መደመር ከችግር ትንተና አንፃር ሀገር በቀል ሲሆን ከመፍትሄ ፍለጋ አንፃር ደግሞ ከሀገር ውስጥም ከውጭም ትምህርት በመውሰድ የተቀመረ መሆኑ በመጽሀፉ ተገልጿል።

በመጽሀፉ ከተሰጠው ብያኔ መረዳት እንደሚቻለው “መደመር” አንድን የላቀ ውጤት ለማሳካት ሀሳባችንን፣ ገንዘባችንን፣ ዕውቀታችንን፣ ሀብታችንን፣ ተግባራችንን፣ ወዘተ. የምንሰበስብበት፣ የምናከማችበት እና የምናካብትበት ሂደት ነው። በዚህም መሰረት፣ “መሰብሰብ” ዛሬ ላይ ያለን እና የተበታተነውን ወደ አንድ ማምጣት ማለት ሲሆን “ማከማቸት” ደግሞ የትላንትን ከዛሬ ጋር አሰናስኖ በአንዱ ላይ ሌላውን መጨመር ማለት ነው። የማከማቸትን ሂደት በቀጣይነት ማከናወንና ማሳካት ለምንፈልገው የላቀ ውጤት የሚያበቃ ወረት (መነሻ አቅም) ማጠራቀም ደግሞ “ማካበት” ይባላል።

በመሆኑም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ መደመር “ሀገር በቀል እውቀትን፤ በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍ፣ በህብረተሰብ፣ በተለያዩ አደረጃጀቶች እና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ በጎንዮሽ እና በተዋረድ ያሉ አቅሞችን እንዲሁም በየአካባቢው የሚገኘውን ሀብት እና ጸጋ አሰባስቦ፣ አቀናጅቶ እና አስተባብሮ በመጠቀም ለሀገር ግንባታና ዘላቂ ተጠቃሚነት የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከት” ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ከሚታዩ ምርቶች እና የግንባታ ውጤቶች ውስጥ አምድ (Column) የብረት፣ ሲሚንቶ፣ አሸዋ፣ ጠጠር እና ውሃ ውህድ መሆኑ እንዲሁም ፕሮጀክት በሶስት ተዋዋይ ወገኖች እና በብዙ ባለድርሻ አካላት ጥምረትና ትብብር የሚተገበር መሆኑ ‘መደመር’ የዘርፉ ተፈጥሯዊ ባህሪ መሆኑ ማሳያ ነው።

## 4.2. የመደመር መሠረታዊያን በኮንስትራክሽን

### 4.2.1. የጋራ ግብና ሀገራዊ ኃላፊነት

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የጋራ ሀገራዊ ኃላፊነት ወስዶ ከመስራት አኳያም ሆነ በተለያዩ ደረጃዎች ተናቦ፣ ተቀናጅቶ እና ተባብሮ ከመስራት አንጻር ሰፊ ክፍተት የሚስተዋልበት እና በመደመር አገላለጽ ጉልህ የብቸኝነት ጉድለት የተጠናወተው ነው። በመሆኑም ግልጽ የጋራ ግብ ማስቀመጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በቀላል አገላለጽ “የአገር ግንባታ” የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የጋራ ግብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሆኖም የአገር ግንባታ የጥቂት ሳይሆን የብዙ አካላት፣ የአንድ ሳይሆን የበርካታ ዘርፎች እንዲሁም ሀገር እንደሚመራ አካል የመንግስት ኃላፊነት በመሆኑ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። በመሆኑም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የጋራ ግብ እና ተልዕኮ “የአገር ግንባታ” ነው ሲባል ሶስት መገለጫዎች አሉት፣

#### 1. ፕሮጀክት

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በአገር ግንባታ ረገድ የሚኖረው ሚና በዋናነት የሚገለጸው በፕሮጀክት ትግበራ ነው። ከትናንሽ ቤቶች እስከ ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች፣ ከመንገድ እስከ ባቡር፣ ከቴሌ እስከ መብራት፣

ከኤርፖርት እስከ ግድብ ሁሉም በፕሮጀክት አግባብ ተቀርጸው የሚተገበሩ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ፕሮጀክቶች ሲተገበሩ የሚገነባው ቤት፣ የሚገነባው ህንጻ፣ የሚገነባው መንገድና ድልድይ፣ ኤርፖርትና የባቡር መስመር አልያም ግድብና መሰረተልማት ብቻ አይደለም። አስተውሎ ለተገነዘበው የሚገነባው ሀገር ነው፤ የምትገነባው ኢትዮጵያ ነች። ይህን በቅጡ መረዳት እና አለመረዳት የሚፈጥረው ልዩነት የትየሌለ ነው።

የእያንዳንዱን ፕሮጀክት ትግበራ ከአገር ግንባታ ጋር አቆራኝቶ ማየት በትግበራ ሂደቱ የሚሳተፉ ተዋንያንን ባህሪ፣ ቁርጠኝነት፣ ትጋት እና ታማኝነት ከመወሰን አኳያ ትልቅ ፋይዳ አለው። ሀገርን መገንባት ከግለሰብ ጥቅም በላይ የሆነ አስተሳሰብን ማዳበር፣ ስራችንን ለላቀ ዓላማ እንደምንሰራ መረዳትን ይጠይቃል። በአንጻሩ ይህንን ሳይገነዘቡ የፕሮጀክት ትግበራን የሚያዘገዩ አካላት የሀገር ግንባታን እንደሚያዘገዩ፤ ከፕሮጀክት የሚሰርቁ ወገኖች ለሀገር ግንባታ የሚውልን ሀብት እንደሚሰርቁ፤ በግድ የሌሽነት የሚሰሩ የገዛ ቤታቸውን በግድየሌሽነት እንደሚገነቡ፤ የሚያበላሹም እንዲሁ የአገር ግንባታ እያበላሹ እንደሆነ ቢረዱት አሁን በዘርፉ የሚስተዋሉ መልካም ያልሆኑ ነገሮች ባይጠፉ እንኳን በዚህ መጠን የተንሰራፉ ባልነበር።

## 2. ተቋም

የተቋም ግንባታ የሀገረ መንግስት ግንባታ የሚጸናበት ዋነኛ መንገድ እንደሆነ ይታወቃል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አገርን የመገንባት የጋራ ግብም ከተቋም አኳያ የሚገለጸው ዘርፉን እና በዘርፉ የሚያዙ እቅዶችን፣ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በውጤታማነት፣ በብቃት፣ በጥራት እና በታማኝነት ማስፈጸም የሚችሉ አስተማማኝ ተቋማት ሲፈጠሩ ነው። መሰል ተቋማትን መፍጠርን በራሱ እንደ ግብ ወስዶ ከመስራት አኳያ ሰፊ ጉድለት ይስተዋላል።

በመሆኑም ጠንካራና አስተማማኝ ተቋማትን መፍጠር በራሱ የኢንዱስትሪው የጋራ ግብ ተደርጎ የሚወሰድ ጉዳይ ነው። የጠንካራ ተቋም ግንባታ ግልጽ አላባዊያን ያሉት እና መለካት የሚችል መሆን ይኖርበታል። ከእነዚህ መካከል የፖሊሲና ህግ ማዕቀፍ፣ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና አመራር፣ የውስጥ አሰራር፣ ቴክኖሎጂና ዲጂታይዜሽን፣ የሥራ ከባቢ እና ተቋማዊ ባህል ወሳኝ ናቸው። በመሆኑም ኢንዱስትሪው "የትም ፍጪው..." በሚል ቢሂል ሳይሆን ከውጤቱ ባሻገር ሂደቱ ላይ በሚጨነቅ፣ በፕሮጀክት ትግበራ ሂደት አስተማማኝ ተቋማዊ ብቃት እየተፈጠረ መሆኑን በሚያረጋግጥ አግባብ ሊመራ እና ሊንቀሳቀስ ይገባል፤ "ምን እያደረግን ነው?" የሚለው ብቻ ሳይሆን "ምን እየሆንን ነው?" የሚለውም ጉዳይ የኢንዱስትሪው የመደመር ብያኔ እና የጋራ ግብ ማጠንጠኛ ነው።

## 3. ኢንዱስትሪ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተለያዩ ተዋንያን የሚሳተፉበት ነው። በተለይም አማካሪ ድርጅቶች፣ የሥራ ተቋራጮች እና በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ባለሙያዎች ቅድሚያ ተጠቃሾች ናቸው። በሴክተሩ የሚሳተፉ ኩባንያዎች እና ባለሙያዎች ብቃት፣ ተወዳዳሪነት፣ ትርፋማነት እና ቀጣይነት ያለው እድገት የሁሉንም አካላት ትኩረት የሚሻው ሌላኛው ወሳኝ የጋራ ግብ ክፍል ነው። ከተቋም ግንባታ አኳያ እንደሚታየው ሁሉ ኩባንያዎቻችን የሀገር ሀብት መሆናቸውን ተገንዝቦ ብቃት ያላቸው፣ ተወዳዳሪ እና ትርፋማ እንዲሆኑ አቅዶ ከመስራት አኳያ የተሰራው ሥራ እምብዛም ነው ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል። ይልቁንም በኢንዱስትሪው ያሉ የኩባንያ ባለቤቶችን የኑሮ ሁኔታና ዘይቤ እየተከታተሉ የማሸማቀቅ፣ እንደ ሀገር ገንቢ ሳይሆን እንደ ሌባ እና ሀገር አፍራሽ የማየት ነገር ያዘነብላል።

የዚህ አመለካከት ምንጭ ሁለት ነው፤ የመጀመሪያው 'ኩባንያዎቹ ጤናማ በሆነ መንገድ አላደጉም' በሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሀገር ሀብት መሆናቸውን በቅጡ ካለመገንዘብ የሚመነጭ ነው።

በመሆኑም፣ የዘርፉ ቁልፍ ተዋንያን ምንም እንኳን የአጭር ጊዜ የፍላጎት ልዩነት ያላቸው ቢመስልም ልዩነትን አጣጥሞና ተሻግሮ፣ ለጋራ ዓላማና ጥቅም መሰለፍ የግድ ይላል። በዚህ ረገድ በተለይ ከግለሰብ ጥቅም በላይ የተቋም/ኩባንያ ጥቅምን፣ ከተቋም/ኩባንያ ጥቅም በላይ ደግሞ የአገርን ጥቅም ማስቀደም እንደ ወሳኝ መርህ ሊወሰድ ይገባል። የተቋምን ጥቅም የሚያሳጣ የግለሰብ ጥቅም ወይም የአገርን ጥቅም የሚያሳጣ የኩባንያ ጥቅም ዘላቂ አይሆንም።

### 4.2.2. ተነሳሽነት

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ጥልቅ እና ውስብስብ ችግር እንዳለበት እንዲሁም በዘርፉ በሚሳተፉ የተለያዩ ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት መካከል ያለው መናበብ፣ ቅንጅት እና የትብብር መንፈስ በሚጠበቀው ልክ እንዳልሆነ እየታወቀ ተነሳሽነቱን ወስዶ ችግሩን በመሰረታዊነት ከመፍታት አኳያ ክፍተት አለ። በተለይም በመንግስት በኩል "የአገር በቀሉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የመንግስትንና የሀገሪቱን የልማት ፍላጎት እንዲሁም ዘላቂ ተጠቃሚነት በመረዳት ተገቢውን እገዛ እያደረገ አይደለም፤ በቀጣይም እምነት የሚጣልበትና ሀገርን የሚያሻግር አይመስልም" የሚል ጥቅል አረዳድና ድምዳሜ ያለ ይመስላል። በዚህም ምክንያት የሴክተሩን ወሳኝ የሚባሉ ተዋንያን አቅርቦ ከመወያየት፣ ከመደገፍ እና እንደአስፈላጊነቱ ከመገሰጽ ይልቅ ገሸሽ የማድረግና በርቀት የመከታተል ነገር ይስተዋላል።

በተመሳሳይ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት ፍላጎታቸውን በሀገር የጋራ ፍላጎት ማእቀፍ ሥር ከማየት እና የመንግስትን መሻት ተረድቶ ከማገዝ ይልቅ የተናጥል አጀንዳቸውን ሲያራምዱ እና በጠባቂነት መንፈስ ሁሌም መንግስትን ሲወቅሱ ይደመጣል። በመደመር አተያይ መሰረት ከዚህ እልህ፣ ኩርፊያ፣ ጠባቂነት እና ከፍዝ ወጥቶ ለመጀመሪያው ግንኙነት ተነሳሽነት መውሰድ፣ እጅን መዘርጋት፣ መቀራረብ፣ መነጋገር እና ለጋራ ግብ መሳካት የሚያግዝ ግልጽ የግንኙነትና አብሮ የመስራት ትልም ማበጀት ይጠይቃል።

# የኮሪደር ልማት እንደ የመደመር እሳቤ ውጤት

5

አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች እየተሰራ ያለው የኮሪደር ልማት ኢኒሺየቲቭ በዋናነት ሁለንተናዊና ዓለም አቀፍ የስማርት ሲቲ ስታንዳርድን ያሟሉ፣ ማህበራዊ አካታችነትንና ተደራሽነትን ያረጋገጡ፣ ዘመናዊና ሰፋፊ የተሽከርካሪ መንገዶችን፣ ተጓዳኝ የብስክሌት እና እግረኛ መንገዶችን እንዲሁም አረንጓዴ ስፍራዎችን እና የህዝብ መዝናኛዎችን በማልማት ለነዋሪዎች የሚመቹ ውብ እና ጽዱ ከተሞችን የመፍጠር ትልም ነው። የኮሪደር ልማቱ ከመንገድ ባሻገር አዋሳኝ የወንዝ ተፋሰሶችን፣ መናፈሻዎችን፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን፣ የህንጻ እድሳትን እና ሌሎች ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚውሉ ሥፍራዎችን ልማት ያቀፈ ነው።

የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ስኬት ልምድ የተወሰደበትና ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች እየተስፋፋ የሚገኝ ነው። በከተማዋ የኮሪደር ልማት የተጀመረበት ዓላማ ቀደም ሲል ከተማዋን የማይመጥኑ ቆሻሻ አካባቢዎች፣ የመሠረተ ልማት ችግር፣ የፍሳሽ ማስወገጃዎች፣ ከደረጃ በታች መሆንና በቂ አለመሆን፤ ዜጎች ከደረጃ በታች የደቀቁ፣ የተጎሳቆሉና ለመኖር በማይመች ሁኔታ ውስጥ እንዲኖሩ የተገደዱበት፣ የእግረኛና

የመኪና መንገዶችና የመኪና ማቆሚያ ሥፍራዎች ችግሮች ይስተዋሉ ስለነበር ይህን ሁኔታ በመሰረታዊነት መቀየር ነው። የኮሪደር ልማቱ ችግሩን መቅረፍ በሚያስችል መልኩ አገልግሎትን በማሳለጥ ለሕዝብ ምቹ፣ የሚዝናናበት የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር ተችሏል። ከተወሰዱ ተሞክሮዎች ውስጥ በምናብ አርቆ የማየት እና በተግባር አልቆ የመስራት ቁርጠኝነት፤ የአመራር፣ የተቋማት፣ የግሉ ዘርፍና የሕዝብ ቅንጅት እና ተናቦ የመሥራት ባህል ጎልቶ የታየበት፤ አጠቃላይ ሂደቱ አሳታፊና አካታች መሆኑ፤ እየተሰራ ያለበት ፍጥነት፣ ስፋት እና ጥራት፤ ሰፊ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ምቹና ጽዱ የከተማ መሠረተ ልማት በመገንባት ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ፍትሃዊ ልማት ለዜጎች ማቅረብ መቻሉ የሚጠቀስ ነው። እነዚህ መገለጫዎች በሙሉ ሊባል በሚቻል ደረጃ የመደመር እሳቤ ነጸብራቆች እና ማሳያዎች ናቸው።

# የተደማሪነት ሳንካዎች በኮንስትራክሽን

6

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለረጅም ጊዜ የተከማቹ ጥልቅ እና ውስብስብ ችግሮች እንዳሉበት ይታወቃል። ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ከመደመር እሳቤ አኳያ ጎልተው የሚታዩ የተደማሪነት ሳንካዎች ሲሆኑ ለእነዚህ ጉዳዮች መፍትሄ ማበጀት በዘርፉ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣትም ሆነ በተለያየ ደረጃ የሚወሰዱ እርምጃዎች ፍሬ እንዲያፈሩ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ወሳኝ ጉዳይ ነው ተብሎ ይታመናል።

## 6.1. የአስተሳሰብ ሳንካዎች

### 1. አለመተማመን

በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚሳተፉ ከፕሮጀክቱ ባለቤት (አሰሪ) ወገን ያሉ፣ የሥራ ተቋራጮች፣ እንዲሁም አማካሪዎች እርስ በእርስም ሆነ በሌሎች ዘንድ በአብዛኛው አመኔታ እና መተማመን የላቸውም። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአስተሳሰብ እና በድርጊት የሚስተዋሉ ሁኔታዎች ሴክተሩን በጥቅሉ “የሌብነት መንደር” የሚል ታፔላ እንዲለጠፍበት አድርጓል። ይህ የሆነው በድንገት ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን ሴክተሩ ከፍተኛ ሀብት የሚንቀሳቀስበትና ለረጅም ዓመታት

ጤናማ ባልሆነ እና ‘በእከክልኝ ልከክልህ’ የግንኙነት መርህ ሲንቀሳቀስ ስለነበረ ነው። ይሁንና በተጨባጭ በሚወሰዱ እርምጃዎች ይህ አስተሳሰብ ከስሩ ካልተነቀለ እና ሴክተሩ በመተማመን እና በትብብር መርህ ላይ ካልተመሰረተ የሚፈለገውን ለውጥና ውጤት ማስመዝገብ አስቸጋሪ ነው። ሀገር በመጠራጠር፣ በባላንጣነት በመተያየት፣ በወቀሳ፣ በክስና በስንፍና ወይም በተናጥል በሚደረግ ሩጫ አይገነባም። ሀገር የሚገነባው በመመካከር፣ በመናበብ፣ በመቀናጀት እና ከምንም በላይ ተማምኖ፣ ተግባብቶ፣ ተባብሮ እና ጠንክሮ በመስራት ነው። የሚታሰበው በመተማመን እና በትብብር ላይ የተመሰረተ ሴክተር በጠንካራ ቁጥጥር እና ተጠያቂነት ካልታገዘ አስተማማኝና ዘላቂ የመሆን እድሉ ትንሽ መሆኑ ፈጽሞ ሊዘነጋ አይገባም።

## 2. ለሀገር በቀል እውቀት እና አቅም ያለን ዝቅተኛ ግምት

ሀገራችን የጥንታዊ ስልጣኔ፣ የበርካታ ሀገር በቀል እውቀቶች እና ልምዶች ብቻ ሳይሆን አሁንም ከፍተኛ እውቀት እና አቅም ያላቸው ዜጎችና ኩባንያዎች ምድር ነች። በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደሚስተዋለው ለሀገር በቀል እውቅት፣ ለሀገር ውስጥ ባለሙያዎቻችን፣ በሀገር ውስጥ አቅም ለተሰሩ የግንባታ ውጤቶች ያለን ግምት ዝቅተኛ ነው። ከራሳችን ይልቅ የውጭውን ማክበር እና የውጭውን ማድነቅ ይቀናናል። ሆኖም፣ ሀገር በውጭ አቅም አይገነባም፤ ለራስ ያለን አመለካከት ማስተካከል እና የራስ አቅምን ማሳደግ የግድ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ የውጭ ባለሙያዎች እና ኩባንያዎች ወደ ሀገራችን እንዳይመጡ ማስቀረት አንችልም፤ ይህን ለማድረግ መሞከር አሁን ከምናስበው እና አገራችንን የዓለም ኢኮኖሚ አካል ለማድረግ እያደረግን ካለነው ጥረት ጋር አብሮ አይሄድም።

በመሆኑም ይሄ እንዲሆን መመኘት ከንቱ ምኞት፣ ይሄ እንዲሆን መድከምም ከንቱ ድካም እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። መፍትሄው ለሀገር በቀል እውቀት እና አቅም ያለንን አተያይ ማስተካከል፣ ብቃት እና ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግ መደገፍ እና ተወዳድረው ማሸነፍ የሚችሉ ባለሙያዎችን እና ኩባንያዎችን መፍጠር ነው።

## 3. የእጥረት አስተሳሰብ

ኢትዮጵያ ትልቅም፣ ብዙ ፀጋዎች ያሏትም ሀገር ናት። ያለመታደል ሆኖ፣ አስተሳሰባችን እያለን እንደሌለን፣ እየቻልን እንደማንችል ነው። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የዚህ የእጥረት አስተሳሰብ ቀጥተኛ ተጎጂ ነው። በተለይም ለተለያዩ ግንባታዎችም ሆነ የመሰረተልማት ዝርጋታዎች መሬት እና የተፈጥሮ የግንባታ ግብአቶች (ድንጋይ፣ አሸዋ፣ እንጨት፣ የተመረጠ አፈር፣ወዘተ.) ማግኘት አዳጋች መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ምክንያት የሚከፈለው ዋጋ እጅግ የተጋነነ መሆኑ ተፈጥሯዊ ያልሆነ እና የእጥረት አስተሳሰብ የፈጠረው ነው። ይህ ጉዳይ በፖሊሲ እና በህግ ተደግፎ በሚሰራ ሥራ መስመር እንዲይዝ ካልተደረገ እንደ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የመሰረተልማት እና ሌሎች ግንባታዎች ጉድለት ባለበት ሀገር የህዝቡንም ሆነ የሀገር የመልማት ፍላጎት ማሟላት ፈታኝ ነው።

## 4. ግድ ማጣት እና አላካኪነት

ይህ ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣ ሲሆን የተለያዩ አካላት መሆን ያለበት ነገር ሳይሆን ሲቀር ወይም መሆን የሌለበት ነገር ሲሆን በ"ምን አገባኝነት እና በምኔ ይነካል" ስሜት ችላ ሲሉት ይስተዋላል።

ይህ ጉዳይ በተለይ በፌደራል ደረጃ በሚሰሩ የመሰረተልማት ፕሮጀክቶች አካባቢ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን ፕሮጀክቶች በአብዛኛው በቀላሉ ሊፈቱ በሚችሉ ምክንያቶች አፈጻጸማቸው ሲጓተት እና ሀገር ላይ ትልቅ ኪሳራ ሲያደርሱ እያዩ እምብዛም ግድ የማይሰጣቸው፤ችግሮችን ተቀናጅቶ በጋራ ከመፍታት ይልቅ ማላከክ የሚቀናቸው የወረዳ፣ የከተማ፣ የክልል እና የፌደራል አካላት በርካታ ናቸው። የዚህ ችግር ምንጭ ኃላፊነትን በሥራ መደብ እና በተቋም አጥር ውስጥ ብቻ ገድቦ መያዝ፣ የሀገራዊ ስሜት መሸርሸር እና ከልክ ያለፈ ግድየለሽነት ነው።

# 6.2. የግብር ሳንካዎች

## 1. ብልሹ አሰራር እና ሌብነት

በዚህ ሰነድ ቀደም ባሉት ክፍሎች እንደተገለጸው የመደመር ብያኔ ማጠንጠኛ ለሀገር ግንባታና ዘላቂ ተጠቃሚነት የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት ዙሪያ ነው፡፡ በአንጻሩ፣ በዘርፉ ባሉ ተዋንያን መካከል የሚኖር ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ማዕከል የሚያደርገው ደግሞ ለግል ጥቅም ሲባል በሀገር ጥቅም ላይ መደራደርን ነው፡፡ በመሆኑም ብልሹ አሰራር እና ሌብነት በተንሰራፋበት ሁኔታ መደመርን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ ተግባራዊ ማድረግ እጅግ በጣም ፈታኝ ነው፡፡ ይልቁንም ይህ ጉዳይ የኢንዱስትሪው ነቀርሳ ተደርጎ የሚወሰድ የመጀመሪያው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የሚስተዋለውን ሌብነት ለመከላከል በሁሉም ደረጃዎችና በተገኙ አጋጣሚዎች ሁሉ ድርጊቱን በተቋምና በአመራር ደረጃ በይፋ ማውገዝ፣ ተጋላጭ ናቸው ተብሎ የሚታመኑ አካላት በሙሉ በግለሰብም ሆነ በኩባንያ ደረጃ በይፋ እንዲያወግዙትና ተጠያቂ እንደሚሆኑ የውዴታ ግዴታ በጽሁፍ እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣ ለሌብነት ተጋላጭ ናቸው ተብለው የተለዩ አካባቢዎችን ሥራ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና የተቀላጠፈ ማድረግ፣ ግልጽነት በየደረጃው እንዲሰፍን ማድረግ፣ ሌብነትን የሚጸየፍና በስነ ምግባር የታነፀ ኢንዱስትሪ መፍጠር፣ ብልሹ አሰራር መፈጸሙ ሲረጋገጥ አስተማሪ እርምጃዎች መውሰድ እና አስተማማኝ የጥቆማ እና የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

## 2. የሥራ ባህል

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተግባራዊ እየተደረጉ በሚገኙ ሀገራዊ ኢኒሺየቲቮች የሥራ ባህል በተጨባጭ እየተለወጠ እንደሆነ እያየን ነው። ሆኖም አሁንም በዘርፉ ያለው የሥራ ባህል እና ተያይዞ የሚታየው የምርታማነት መጠን ዝቅተኛ ነው። በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ አሁን ኢኒሺየቲቮች አካባቢ የሚታየውን የሥራ ባህል ማስፋትና ሀገራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 3. ለጥራት የሚሰጥ ዋጋ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሌላኛው ስብራት እና የመደመር ሳንካ ለጥራትና ውበት የሚሰጥ ዝቅተኛ ቦታ ነው። ኢንዱስትሪው ከጥራት እና ውበት ጋር በተያያዘ “ዋናው መሰራቱ ነው”፣ ”ደግሞ ለእኛ ይሄ አንሶ ነው?!”፣ “ካገለገለ…”፣ “ምን ችግር አለው?”ወዘተ. በሚሉ ጥራትን እና ውበትን አሳንሰው በሚያዩ ብሂሎች የተከበበ ነው። በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ኢኒሺየቲቭ በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ላይ በተጨባጭ ማየት እንደተቻለው ውበትን ከጥራት እና ፍጥነት ጋር አጣጥሞ ፕሮጀክቶችን መተግበር ይቻላል። በተመሳሳይ ይህንን ተሞክሮ የሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገለጫ ማድረግ ያስፈልጋል።

# በመደመር እሳቤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተልዕኮ

7

በመደመር እሳቤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተልዕኮ “በጋራ፣ ኢትዮጵያን እንገነባለን! በብቃት፣ በጥራት፣ በታማኝነት” የሚል ነው። ተደጋግሞ እንደተገለጸው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በባህሪው የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን መናበብ፣ ቅንጅትና ትብብር ይጠይቃል። ለኢንዱስትሪው በጋራ መስራት፣ መቀናጀት እና ከምንም በላይ ደግሞ መተባበር የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው። መተባበርና መደጋገፍ ማለት ግን የአንዱን ሚና ሌላው ይውሰድ ማለት በፍጹም አይደለም፤ ሁሉም አካል ሚናውን አውቆ እና ተረድቶ ግዴታውን መወጣት፣ በገባው ግዴታ ልክም መጠየቅ ይኖርበታል። እያንዳንዱ የሚተገበር ፕሮጀክት በዚህ እሳቤ ከተቃኘ እና ከተመራ ብዙ አስደናቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ ይቻላል። በዘርፉ ያሉ ተዋንያን በሙሉ ይህን እውነታ በቅጡ እስካልተረዱት እና በዚህ መልክ እስካላሰቡ ድረስ በዘርፉ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት አስቸጋሪ ነው። ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እመርታ ሁለንተናዊ ትብብር ወሳኝ እና የማይተካ ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወሳኝ መገለጫዎች ሊሆኑ የሚገባቸው መርሆች ወይም ማዕዘናት ብቃት፣ ጥራት እና ታማኝነት ናቸው። እነዚህን ጉዳዮች አስማምቶ እና ሚዛን ጠብቆ መጓዝ

ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ህልውና የመጨረሻው ዋስትና ነው። ‘ብቃት’ ስንል ውድድር፣ ብቃት ስንል ተወዳዳሪነት፣ ብቃት ስንል ፕሮጀክትን በተያዘለት ጊዜ እና ወጪ ማጠናቀቅ መቻል ነው። በመሆኑም ብቃት አንዱ የኢንዱስትሪው መገለጫ እና ወሳኝ ማእዘን ነው። ይህ እንዲሆን በኢንዱስትሪው ውስጥ የተሰማራውን እና የሚሰማራውን የሰው ኃይል ብቃት (በአስተሳሰብ፣በእውቀትና በክህሎት) ማሳደግ፣ አሰራራችንን ማዘመን፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ ዘመናዊ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስርዓትን መከተል የግድ ያስፈልጋል። በድጋሚ ለማለት ያህል፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ህልውና እና አስተማማኝ እድገት ዋስትና ብቁ እና ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ነው።

በተመሳሳይ፣ ‘ጥራት’ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መለያ መሆን አለበት ሲባል፣ ግንባታዎቻችን በእይታ ረገድ ውበትን የተላበሱ፣ ከአገልግሎት አንጻር በጊዜ ተፈትነው የሚያልፉና ትውልድን የሚሻገሩ፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያከብሩ፣ ደህንነታቸው የተረጋገጡ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ እና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይገባል ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ‘ታማኝነት’ ልንገነባው የምንፈልገው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሌላኛው ወሳኝ የማዕዘን ድንጋይ ነው። ታማኝነት በባለሙያም፣ በኩባንያም ደረጃ አስፈላጊ ነው። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዲስተካከል፣ ከህመሙ እንዲያገግም እና በመንግስት በኩልም ተገቢው ድጋፍ እንዲደረግለት ከተፈለገ የዘርፉ ተዋንያን ጤናማ ያልሆነ ግንኙነትን ማስወገድ እና ሌብነትን በይፋ መቃወም አለብን። በኢንዱስትሪው ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም ባለሚና አካላት የማይገባቸውን የማይጠይቁ መብታቸውን ደግሞ አሳልፈው የማይሰጡ እና በገንዘብ የማይሸምቱ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

በሁሉም አቅጣጫዎች እና ደረጃዎች የሚገኙ የኢንዱስትሪው ባለድርሻ አካላት በጋራ፣ ተቀራርበው እና ተባብረው መስራት ከቻሉ አሁን ላይ የሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮችን መሻገር፣ ተግዳሮቶችን ወደ እድል መቀየር ይቻላል። በመንግስት ደረጃ የሀገር ውስጥ ፍላጎቶችን ማርካት ብቻ ሳይሆን በኢንዱስትሪው ያሉ ኩባንያዎች ከአገር ወጥተው በጎረቤት አገራት እና በሌሎች የአፍሪካ አገራት ገበያዎች ጭምር መወዳደር፣ መሳተፍ እና ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ማመንጨት የሚችሉ ጠንካራ የአገር አምባሳደሮች እንዲሆኑ አስቦ እና አቅዶ መስራት ያስፈልጋል።

# በኢንዱስትሪው ውስጥ በመደመር እሳቤ ተቃኝተው ሊተገበሩ የሚችሉ ኢኒሺየቲቮች

# 8

## 8.1. የመሰረተልማት ፕሮጀክቶችን ኢንቨስትመንት ውጤታማነት እና ብቃት ማሻሻል

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአገራዊ ጥቅል ምርት አንጻር ለመሰረተልማት ዝርጋታ ከፍተኛ በጀት ከሚመድቡ ቀዳሚ ሀገራት ተርታ ትመደባለች። በዚህም መሰረት በየዓመቱ ከአገራዊ ጥቅል ምርት እስከ 15 በመቶ እና ከዚያ በላይ በጀት በመመደብ እንደ መንገድ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ያሉ የተለያዩ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ይገነባሉ። ሆኖም ግን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ይህ በመቶ ቢሊዮኖች የሚደረግ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የውጤታማነት እና የብቃት ጥያቄ ይነሳበታል። በተለይም "የፕሮጀክቶች ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጤናማ ባልሆነ መንገድ እየናረ ነው"፣ "የሚገነቡ መሰረተልማቶችም የታለመላቸውን ዓላማ እና ግብ በሚጠበቀው ልክ አያሳኩም" የሚለው አስተያየት ጎልቶ ይሰማል። ምንም እንኳን ትክክለኛ መጠኑን ለማወቅ በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሰረተ ትንተና ቢያስፈልግም አስተያየቱ ከእውነታው ብዙም የራቀ እንደማይሆን የሚያመላክቱ ምልክቶች አሉ። በትግበራ ላይ ያሉ የመሰረተልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ከጊዜ እና ከወጪ አኳያ ማየት ብቻ ለዚህ በቂ ማሳያ ሊሆን ይችላል፤ ከተያዘላቸው ጊዜና በጀት ከመቶ ፐርሰንት በላይ ተጨማሪ ጊዜና ወጪ የሚያስወጡ ፕሮጀክቶች በርካታ ናቸው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ እንደ ሀገር ያለው የመሰረተልማት ጉድለት እና በተጨማሪነት የሚያስፈልገው በጀት በጣም ከፍተኛ ነው። የተለያዩ የጥናት ውጤቶች እና ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት የሀገሪቱን የመሰረተልማት ፍላጎት ለማሟላት በየዓመቱ እስከ አራት መቶ ቢሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ ተጨማሪ በጀት ኢንቨስት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ታሳቢ ሲደረግ የመሰረተልማት ፕሮጀክቶችን ኢንቨስትመንት ውጤታማነት እና ብቃት ማሻሻል የግድ መሆኑን ያመላክታል። በመሆኑም የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት እና ለአምራች ክፍለ ኢኮኖሚው የሚኖራቸውን ፋይዳ በጥልቀት መፈተሽ እንዲሁም የግንባታ ደረጃቸውን እና ወሰናቸውን በዚሁ አግባብ መወሰን ያስፈልጋል። በተጨማሪም መሰረተልማት በራሱ ግብ ላይሆን ስለሚችል የተዘረጋውን መሰረተልማት በውጤታማነት ከመጠቀም አኳያ ጠንካራ ክትትል ማድረግ እና አዋጭ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ይገባል። በተመሳሳይ የፕሮጀክቶች ትግበራ በመደመር እሳቤ ቢቃኝ እና ሁሉም የሚመለከተው አካል ለጋራ ሀገራዊ ግብ ተግባብቶ፣ ተናቦ፣ ተቀናጅቶ እና ተባብሮ መስራት ቢቻል አሁን ያለውን የኢንቨስትመንት ብቃት ደረጃ ትርጉም ባለው መልኩ ማሻሻል ይቻላል።

## 8.2. የሀገር አምባሳደር መሆን የሚችሉ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን ማፍራት

እንደ የመንገድ ዘርፍ እና ቤቶች ልማት ያሉ ፕሮግራሞች የአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን አቅም በማሳደግ በኩል የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ለማሳያ ያህልም የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በ1989 ዓ.ም. ሲጀመር በከፍተኛ የመንገድ ሥራ ሊሳተፍ የሚችል የአገር ውስጥ ተቋራጭ ማግኘት አይታሰብም ነበር። የአገር በቀል ተቋራጮች (የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ጨምሮ) ከሁለት

አስርት ዓመታት በኋላ በፌደራል መንግስት ከሚሰሩ የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ በገንዘብ እስከ 60 በመቶ፣ በፕሮጀክት ብዛት ደግሞ እስከ 80 በመቶ የሚሆነውን ኮንትራት በመፈረም እየተሳተፉ ነው፡፡ ይህ አንጻራዊ “ስኬት” እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ ተቋራጮች አቅም፣ ውጤታማነት እና አስተማማኝነት አሳሳቢና ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ተወዳዳሪነት መለኪያ (Excellence Score) ከታየ የአገር ውስጥ ተቋራጮች በዚሁ አገር እየተንቀሳቀሱ ካሉ የቻይና ተቋራጮች ጋር ሲወዳደሩ የሚያስመዘግቡት ደረጃ እስከ 1/3ኛ ነው፡፡

በተጨማሪም ተቋራጮቻችን እንደ ኩባንያ ከአገራቸው ውጭ በመሄድ ተሳትፈው ተወዳዳሪ እየሆኑ አይደለም፡፡ እንደ እኛ ላለ ትልቅ አገር ከውጭ በሚመጡ ተቋራጮች ላይ ተመክተን ሥራችንን ማቀድ የሚያስኬድ ካለመሆኑም በላይ የአገራችን ኩባንያዎች ተወዳዳሪ ሆነው ቢያንስ በምስራቅ አፍሪካ እና በአህጉር ደረጃ ያሉ እድሎችን መጠቀም የሚያስችል ስልታዊ አካሄድ መከተል ይኖርብናል፡፡ ከዚህ አኳያ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች የሚመዘኑበት እና እውቅና የሚሰጥበት ማዕቀፍ (DCI Competitiveness Rating and Award Mechanism) በማዘጋጀት፣ የኢንዱስትሪው ተዋናዮችን ተወዳዳሪነት በመፈተሽና በመመዘን በሚቀጥለው 5 ዓመታት ውስጥ ቢያንስ 10 ተቋራጮች እና 10 አማካሪዎች የሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አምባሳደር ሆነው በጎረቤት ሀገራት እና በአፍሪካ ደረጃ መወዳደር እና መሳተፍ እንዲችሉ በመንግስት ደረጃ እውቅና ተሰጥቶት የተለየ ክትትል እና እገዛ ማድረግ ይቻላል፡፡

## 8.3. በሀገራዊ ኃላፊነት እና በአርበኝነት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን መቅረጽ

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሰረተልማት ፕሮጀክት ብቻ አይደለም። ግድቡ ሀገራዊ ቁጭት፣ ኅብርና አንድነት እንዲሁም ብሔራዊነት ዐርበኝነትበጉልህ የታየበትና የተገለጠበት፣ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ የጎላ አበርክቶ ያለው፣ እንደ ሀገር የጂኦፖለቲካልና ዲፕሎማሲ ጫናዎችን ድል ያደረግንበት፣ የይቻላል መንፈስን የፈጠረ ታሪክ ቀያሪ ፕሮጀክት ነው። በየዘርፉ መሰል ፕሮጀክቶች በጥልቅ ጥናት እና ጥንቃቄ ተለይተው ቢተገበሩ የሚኖራቸው ፋይዳ ጉልህ ነው። በዚህ ረገድ እንደ አፈር ማዳበሪያ ያሉ ወሳኝ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት የተጀመረው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ አቅጣጫዎች የሚወጡ የፍጥነት መንገዶችን /Expressways/፣ የባቡር መስመሮችን፣ ወዘተ. የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን አስተባብሮና አቀናጅቶ፣ በብሔራዊ ዐርበኝነት ስሜት መተግበር ቢቻል ልክ እንደ ህዳሴው ግድብ ታሪክ ቀያሪ የመሆን አቅም አለው።

## 8.4. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የእርስበርስ እንዲሁም የመንግስትን እና የግል አጋርነትን ማጠናከር

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ካሉበት ጉድለቶች ውስጥ ፋይናንስ አንዱ ነው። ይህን ጉድለት ለመሙላት የመንግስት እና የግል ዘርፉ አጋርነት አንዱ ነው። ከዚህ አንጻር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባ ደረጃ እየተለመደ የመጣው በቤቶች ልማት እና በከተሞች አካባቢ በትላልቅ ህንጻዎች (ሞሎች) ግንባታ እየታየ ያለው ትብብር በማሳያነት ሊወሰድ ይችላል።

ይህንን ተሞክሮ በመንገዶች፣ በድልድዮች፣ በኃይል ማመንጫ እና ሌሎች መሰረተልማቶች ግንባታ ማስፋት ይቻላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞው የሀገራችን የሥራ ተቋራጮች ከግለኝነት አስተሳሰብ ወጥተው በእሽሙር ማኅበራት (JV) ወይም በተለያዩ መንገዶች እየታጠመሩ ከመንግስት ጋር ተባብረው ትላልቅ ፕሮጀክቶችን የሚሰሩበት እና በጋራ የሚያድጉበትን መንገድ ቢያስቡ ሀገራዊ ፋይዳው የጎላ ነው። ይህን በአግባቡ አቅዶ መስራት የግሉን ባለሀብት እውቀት፣ ገንዘብ እና ክህሎት በማሰባሰብ፣ በማከማቸት እና በማካበት መደመርን በኮንስትራክሽን ዘርፍ ተግባራዊ ለማድረግ አንዱ መንገድ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

## 8.5. ከውጭ የሚገኝ ድጋፍን በአገር ውስጥ የማስቀረት ውጥን

የሀገራችን የመሰረተልማት ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ፍላጎት በአብዛኛው ከሀገር ውስጥ ምንጮች በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ከልማት አጋሮች እንደሚገኝ ይታወቃል። ከውጭ በሚገኙ የፋይናንስ ድጋፎች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በአብዛኛው ከውጭ በሚመጡ ኩባንያዎች የሚተገበሩ ሲሆን ይህም ከውጭ የመጣው ካፒታል በአብዛኛው ተመልሶ እንዲወጣ ከማድረጉም በላይ የአገር ውስጥ ኩባንያዎች በትላልቅ ፕሮጀክቶች ያላቸው ተሳትፎ እንዲገደብ አድርጓል። እንደ ቻይና ያሉ ሀገራት እኛ አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ ላይ በነበሩበት ወቅት በተመሳሳይ ከአለምቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ለመሰረተልማት የሚሆን ብድርና እርዳታ ይወስዱ የነበረ ሲሆን አጠቃቀማቸው ግን አሁን እኛ እየተጠቀምንበት ካለው ፍጹም የተለየ ነበር። በወቅቱ የተገኘውን የፋይናንስ ድጋፍ መሰረተልማታቸውን ለመገንባት ብቻ ሳይሆን የኩባንያዎቻቸውን አቅምም ለማሳደግ ስለተጠቀሙበት ዛሬ ላይ የቻይና ኩባንያዎች አገራቸውን ከመገንባት ተሻግረው በመላው ዓለም መሰራጨት እና ተወዳዳሪ መሆን ችለዋል።

ከዚህ ተሞክሮ በመቅሰም እንደ መንግስት እና እንደ ሀገር ከልማት አጋሮች የሚገኙ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠሩ ድጋፎችን ከመሰረተልማት ግንባታ ባሻገር የራሳችንን አቅም ለመገንባት እንዴት መጠቀም እንደምንችል ማሰብ፣ መጨነቅ እና ሊተገበር የሚችል ስልት ማዘጋጀት ይኖርብናል።

## 8.6. የገጠር መሰረተልማትን ማስፋፋት

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የመደመር እሳቤ በተሟላ መልኩ ሊተገበር ከሚችልባቸው አካባቢዎች ውስጥ የገጠር መሰረተልማትን ማስፋፋት አንዱና ዋናው ነው። በአገራችን የገጠር አካባቢ ያለው አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ እና ደረጃ ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ በበርካታ ችግሮች የተከበበ ነው። ነዋሪዎች በቂ የሆነ አማራጭ የገቢ ማስገኛና ኑሮ መደጎሚያ መንገዶች የሌላቸው ሲሆን በዛው ልክ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ያላቸው ተደራሽነት በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በገጠር ቀበሌዎች እና መንደሮች የሚሰሩ የልማት ሥራዎች በቅንጅት ታቅደው የሚተገበሩ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል እና ሊያድግ በሚችል መልኩ ሰፊ መሠረት ኖሯቸው የሚጀመሩ ባለመሆኑ ብዙውን ጊዜ የገጠሩ ህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ በፍጥነት ሲለወጥ አይስተዋልም።

በመሆኑም የገጠር ቀበሌዎችን እና መንደሮችን አስቀድሞ በታቀደ እና በተቀናጀ መልኩ በሂደት ወደ ከተሜነት ሊያሸጋግር በሚችል መልኩ መሠረት እየጣሉ መሄድ ያስፈልጋል። ይህንንም ከገጠር መሬት የሚገኘውን ውጤታማነትና ጥቅም የላቀ ማድረግ በሚያስችል የመሬት አጠቃቀም እቅድ አስደግፎ እንዲሁም የተቀናጀ የገጠር መሠረተ ልማቶችንና ማህበራዊ አገልግሎቶችን እቅድ ማእከል አድርጎ መተግበር ይቻላል።

ለዚህም እንዲያግዝ የገጠር ቀበሌዎችንና መንደሮችን የዕድገት አቅጣጫ የሚጠቁም፣ በቀላሉ መሠረተልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማካተት የሚያስችል የተቀናጀ የኮሪደር ልማት እቅድ ማዕቀፍ /Integrated Corridor Development Plan Framework/ ሊዘጋጅ ይገባል። በመላ አገሪቱ ከሚገኙ ከ10 ሺ በላይ የገጠር ቀበሌዎች (ከ20 ሺ በላይ የገጠር የልማት ማዕከላት) በቀጣይ አምስት ዓመታት ቢያንስ 60 በመቶው ላይ ይህን የተቀናጀ እቅድ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በገጠር የሚኖረው ህዝብ ከኑሮ መሠረቱ (ከማሳው/ከእንስሳት እርባታው፣ ወ.ዘ.ተ) ብዙም ሳይርቅ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኝ እና ኑሮውን ትርጉም ባለው ደረጃ እንዲያሻሽል ማድረግ ይቻላል።

የተቀናጀ የገጠር ኮሪደር ልማት ዕቅድ የመደመር እሳቤን በተጨባጭ ወደ መሬት ለማውረድ አይነተኛ መሳሪያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ከመሆኑም በላይ በየአካባቢው ያለውን ፀጋና አቅም በመጠቀም እንደ ሀገር የተቀመጠውን የብልጽግና ራዕይ ሰፊውን የአርሶ አደር፣ አርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር የህብረተሰብ ክፍል ባሳተፈ፣ ማዕከል ባደረገ እና ባቀፈ መልኩ ለማሳካት ያስችላል። ከዚህም በላይ ህብረተሰቡ በልማቱ ሥራ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ የመሪነት ሚና እንዲጫወት በማድረግ ማህበራዊ መስተጋብርን ማዳበር እና ወረት ማካበት ይቻላል።

## 8.7. ንጹህ እና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መፍጠር

ተደጋግሞ እንደተገለጸው ብልሹ አሰራር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መገለጫ የሆነ ይመስላል። ሆኖም ደግሞ ደጋግሞ "ኢንዱስትሪው ተበላሽቷል፣ ኢንዱስትሪው የሌባ ስብስብ ነው" በማለት የሚቀየር ነገር አይኖርም።

ይልቁንም ንጹህ እና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ /Clean and Competitive Construction Industry/ እንዴት ሊገነባ እንደሚችል አስቦ እና አቅዶ መስራት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉ ባለሚና አካላትን መቀራረብ፣ መግባባት እና መተባበር ይጠይቃል። ከዚህ አኳያ በብዙ ሀገራት እንደተለመደው በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሳተፉ ባለሙያዎች በሙሉ የሚገዙበት Code of Conduct for Construction Professionals ተዘጋጅቶ፣ የጋራ መግባባት ተደርሶበት እና የማይታለፍ የዘርፉ ቀይ መስመር ሆኖ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል። ስለሆነም ቅድሚያ ተነሳሽነቱን ወስዶ እና ራሱን የቻለ ኢኒሺየቲቭ ቀርጾ ንጹህ እና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመፍጠር የሚያስችል ይፋዊ የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 8.8. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን መናበብ፣ ቅንጅት እና ትብብር የሚያጠናክሩ አደረጃጀቶችን መፍጠርና ማጠናከር

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሀገራችን እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ሲያበረክት የቆየ እና በቀጣይም ማሳካት ለምንፈልገው ብልጽግና የማይተካ ሚና ያለው ዘርፍ ከመሆኑም ባሻገር ግዙፍና በርካታ ተዋናዮች ያሉበት ነው። በመሆኑም በኢንዱስትሪው ውስጥ ባሉ ባለሚና አካላት መካከል የሚኖር መናበብ፣ ቅንጅት እና ትብብር እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው በጠንካራ አደረጃጀት እና አሰራር ሲታገዝ ነው። ለማሳያ ያህልም በዘርፉ የሚካሄዱ የምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ከልማት ፕሮጀክቶች ጋር ለማስተሳሰር እንዲሁም የዘርፉን የሰው ኃይል ስምሪት ውጤታማ ለማድረግ በዩኒቨርስቲዎች፣ በስልጠናና የምርምር ተቋማት፣ በኢንዱስትሪው እና በመንግስት መካከል ጠንካራ ትስስር መፍጠር ወሳኝ እና የግድ ነው።

በመሆኑም ጠንካራና ውጤታማ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ካውንስል፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፎረም፣ የመንገድ ሴክተር ጉባኤ፣ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ፎረም ወዘተ. ያሉ አደረጃጀቶችን መፍጠርና በተጠናከረ አግባብ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

# ማጠቃለያ

9

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የኢትዮጵያ ብልጽግና መሰረት እና ምሶሶ እንዲሁም የሀገራዊ ኩራት ምንጭ ሊሆን የሚችልበት ከፍተኛ አቅም አለው። ይህ እንዲሆን ግን በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር መስተካከል ያለባቸው ወሳኝ ጉዳዮች አሉ። እነዚህ ጉዳዮች በጥልቀት ሲታዩ በመደመር እሳቤ ሊገለጹ እና ሊጠቃለሉ ይችላሉ። በመሆኑም የመደመር እሳቤን በአግባቡ ተረድቶ እና በዝርዝር ተንትኖ ወደ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማምጣት፣ የኢንዱስትሪውን እንቅስቃሴ እና አመራር በመደመር እሳቤ መቃኘት እና ወደ መሬት ማውረድ ከዘርፉ የምንጠብቀውን ውጤት ለማግኘት ያስችለናል።

Ministry of Urban & Infrastructure

# መደመር በኮንስትራክሽን

www.mui.gov.et